**በፕሬዘደንት ዲየትር ኤፍ ኡክዶርፍ**
*የቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ*



# በክርስቶስ ፍቅር አለምን ሙሏት

ስለ ገና በአል ስናስብ፣ በአብዛኛው ስጦታዎችን ስለ መስጠት እና ስለ መቀበል እናስባለን። ስጦታዎች ከፍተኛ ዋጋ የምንሰጣቸው የባህል ክፍል ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን የወቅቱን ክቡርነት ሊቀንሱ እናም ትርጉም ባለው መንገድ የአዳኛችንን ልደት ከማክበር ሊያውኩን ይችላል።

ከግል ልምዴ እንደማውቀው በጣም የሚታወሱት የገና በአሎች በጣም ትሁት የሆኑት ናቸው። የህፃንነቴ ስጦታዎች በዛሬ ጊዜ መለኪያ ዎች በእርግጠኝነት ያልተብለጨለጩ ነበሩ። አንድ አንድ ጊዜ የተሰፋ ሸሚዝ ወይም ጓንቶች ወይም ካልሲዎች ተቀብያለው። ወንድሜ እራሱ ከእንጨት የቀረጸውን ቢላ ሰጥቶኝ የነበረነትን አንድ ለየት ያለ የገና በአል አስታውሳለው።

የገና በአልን ትርጉም ያለው ለማድረግ ውድ የሆኑ ስጦታዎችን አይጠይቅም። ከ 1987 እስከ 1992 (እ.አ.አ) እንደ ሰባ ጉባኤ አባል ባገለገለው የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ግሌን ኤል ረድ የተነገረውን ታሪክ አስታወስኩ። ከብዙ አመታት በፊት በገና በአል ዋዜማ ላይ፣ የኤጲስ ቆጶስ ግምጃ ቤትን እየተቆጣጠረ ሳለ፣ ወደ ከተማው በቅርቡ ስለመጡ ችግረኛ ቤተሰብ ከአንድ የቤተክርስቲያን መሪ ሰማ። ትንሹን የመኖሪያ ቦታቸውን ለመጎብኘት ሲሄድ፣ አንድ ባል የሌላት ወጣት እናት ከ10 አመት በታች ከሆኑ አራት ልጆች ጋር አገኘ።

የቤተሰቡ ችግርተኝነት በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ በዛ የገና በአል እናት ለልጆቿ ስጦታዎችን መግዛት አልቻለችም ነበር፤ የገና ዛፍም እንኳን መግዛት አልቻለችም። ወንድም ረድ ከዛ ቤተሰብ ጋር ተነጋገረ እናም ሶስቱ ትንንሽ ሴት ልጆች አሻንጉሊት ወይም በእንስሳት ቅርፅ የተሰሩ መጫወቻዎችን እንደሚወዱ አወቀ። ስድስት አመት የሆነውን ወንድ ልጅ ምን እንደሚፈልግ ሲጠይቅ፣ የራበው ትንሽዬ ልጅ እንዲህ ብሎ መለሰ፣ "አንድ ጎድጓዳ ሳህን የተከካ አጃ ሾርባ እፈልጋለሁ።"

ወንድም ረድ ትንሹን ልጅ የተከካ የአጃ ሾርባ እናም ምናልባት ሌላ ነገር ቃል ገባለት። ከዛ ወደ ኤጲስ ቆጶሱ ግምጃ ቤት ሄደ እና የዛን ቤተ ሰብ አፋጣኝ ፍላጎት ለማሟላት ምግብና ሌሎች አቅርቦቶችን ሰበሰበ።

በዛ ጠዋት አንድ ቸር የኋለኛው ቀን ቅዱስ 50 ዶላረ "ለተቸገረ ሰው" ብላ ሰጥታው ነበር። ያንን መዋጮ በመጠቀም ወንድም ረድ ሶስቱን የራሱን ልጆች ይዞ የገና በአል ግብይት ሄደ—ልጆቹ ለተቸገሩት ልጆች መጫወቻዎችን መረጡ።

መኪናውን በምግብ፣ በአልባሳት፣ በስጦታዎች፣ በገና ዛፍ እና በአ ንድ አንድ ጌጣጌጦችን ከጫኑት በኋላ ረዶቹ ወደ እነዛ ቤተሰብ መኖሪያ በመኪና ተጓዙ። እዛ እናትዬዋን እና ልጆቿን የገና ዛፉን በማስተካከል አገዙ። ከዛም ከስሩ ስጦታዎችን አስቀመጡ እናም ለትንሹ ልጅ ትልቅ እሽግ የተከካ አጃ ስጦታ ሰጡት።

እናትዬዋ አነባች፣ ልጆቹ ተደሰቱ እናም ሁሉም የገና መዝሙር ዘመሩ። በዛ ምሽት የረድ ቤተሰብ ለእራት ሲሰበሰቡ፣ ለሌላ ቤተሰብ የገና ደስታን ስላመጡ እንዲሁም ትንሹ ልጅ አንድ ጎድጓዳ ሳህን የተከካ የአጃ ሾርባ እንዲቀበል ለማግውዝ ስለቻሉ ምስጋና አቀረቡ።[1]

## ክርስቶስ እና የመስጠት መንፈስ

የሰማይ አባታችን የልጁን ልደት ለማክበር የመረጠውን ቀላሉን ነገር ግን ክብር ያለውን መንገዶች አስቡ። በዛ በተቀደሰ ምሽት፣ መልአክቶች ለሀብታሞች ሳይሆን ለእረኞች ተገለፁ። ልጅ ክርስቶስ በትልቅ ቤት ውስጥ ሳይሆን በግርግም ውስጥ ተወለደ። በሀር ሳይሆን በመጠቅለያ ጨርቅ ተጠቀለለ።

የዛ የመጀመሪያው የገና በአል ቀለል ማለት የአዳኙን ሕይወት ጠቆመ። ምንም እንኳን መሬትን ቢፈጥርም፣ በግርማዊ ግዛቶች እና በክ ብር ውስጥ ቢራመድም፣ በአብ ቀኝ እጅ ቢቆምም፣ የሚረዳ እንደሌለው ልጅ ወደ ምድር መጣ። ሕይወቱ የትሁት ባላባትነት ሞዴል ነበር፣ እና በድሆች፣ በታመሙት፣ ባዘኑት እና ሸክማቸው በከበደ መሀል ሄደ።

ምንም እንኳን ንጉስ ቢሆንም፣ ስለ ክብርም ሆነ ስለሰዎች ሀብት አልተጨነቀም። ሕይወቱ፣ ቃሎቹ እና የቀን ለቀን ተግባሮቹ ቀለል ያሉ ነገር ግን ታላቅ የሆኑ የክብር ሀውልቶች ነበሩ።

እንዴት መስጠት እንዳለበት ፍፁም በሆነ ሁኔታ ያወቀው ክርስቶስ ኢየሱስ የመስጠትን መንገድ አስቀመጠልን። በብቸኝነትና በሀዘን ልባቸው ለከበደ ሰዎች፣ ርህራሄንና መፅናናትን ያመጣል። በህመምና በስቃይ አካላቸውና አእምሮአቸው ለተጎዱ ሰዎች፣ ፍቅርንና ፈውስን ያመጣል። ነፍሳቸው በሀጢያት ለተጫነ ሰዎች፣ ተስፋን፣ ይቅርታን እና መዳንን ያቀርባል።

አዳኛችን በእኛ መሀል ቢሆን፣ ሁሌም በነበረበት ቦታ የዋሆችን፣ አዛኞችን፣ ትሁቶችን፣ በጭንቀት ላይ ያሉትን እና የመንፈስ ድሆችን እያገለገለ እናገኘው ነበር ። በዚህ የገና በአል ወቅትና ሁሌም እሱ እንደሚወደው በመውደድ ለእርሱ እንስጥ። የልደቱን ትሁት ክብር፣ ስጦታዎች እና ሕይወት እናስታውስ። በቀላል የደግነት፣ የልግስና እና የርህራሄ ተግባሮች አማካኝነት በፍቅሩ ብርሀን እና የመፈወስ ኃይሉ አለምን እንሙላት።

ማስታወሻ

1.1. ግሌን ኤል ረድ *Pure Religion: The Story of Church Welfare since 1930 (እ.ኦ.አ)* (1995), 352–53፤ እንዲሁም ግሌን ኤል ረድ፣ "A Bowl of Oatmeal," *Church News*፣ ታህሳስ 2፣ 2006 (እ.አ.አ)፣ 16።

### ከዚህ መልእክት ማስተማር

ፕሬዘደንት ኡክዶርፍ የአዳኙን የመስጠት መንገድ መከተል እዳለብን አስተማሩ። የምትጎበኙትን ሰዎች ተራ በተራ አዳኙ የሰጣቸውን ስጦታ እዲጠሩ መጠየቅን አስቡ፣ እናም ያንን ስጦታ ሌሎችን ለማገልገል እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ተወያዩ። ለምሳሌ፣ አንድ አባል በሙዚቃ ስልጠና ተባርኮ ከነበረ፣ እሱ ወይም እሷ ወደ አንድ አንድ ጎረቤቶች በመሄድ የገና መዝሙር መዘመር ይችላል/ትችላለች። ከምትጎበኟቸው ሰዎች ጋር የትኛውን ስጦታ ለማካፈል፣ እንዴት ማካፈል እንደሚችሉ እና ለማን ማካፈል እንዳለባቸው እንዲያውቁ መንፈሳዊ ማነሳሻ ለመጠየቅ በፀሎት እንዲበረከኩ ማቅረብ ትችላላችሁ ። በምትቀበሉት ማንኛውም መንፈሳዊ ማነሳሻ ላይ ክትትል አድርጉ።

## ወጣቶች

### ከሌሎች ልምድ ተማሩ

ፕሬዝደንት ኡክዶርፍ "በጣም የሚታወሱት የገና በአሎች በጣም ትሁታማ መሆን የሚችሉት ናቸው" ብለው ሲያስተምሩ ከግል ልምዳቸው ተናገሩ ። ካለፉት ትውልዶች በጣም ብዙ ነገሮች መማር እንችላለን፤ ብዙ ጎልማሳዎች በጦርነት ጊዜያት፣ ያለስራ፣ በህመም ወይም ሌሎች ፈተናዎች ውስጥ ኖረዋል። የቆዩ የዋርድ ወይም የቅርንጫፍ አባሎችን ስላሳለፉት በጣም ትርጉም ያለው የገና በአል እንዲነግሯችሁ ጠይቁ። ታሪካቸውን መፃፍ ትችላላችሁ። በዚኛው የገና በአል የበለጠ ከልብ የመነጨ አገልግሎት መስጠቱ ላይ እና አዳኙን ማስታወሱ ላይ በማተኮር ከእነርሱ ምሳሌ ለመማር ሞክሩ።

## ልጆች

### ከኢየሱስ ክርስቶስ የመጡ ስጦታዎች

አንድ አንድ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት ለማክበር የገና ዛፍን ይጠቀማሉ። አንድ አንድ ጊዜ ሰዎች የሌሎችን ስጦታዎች ከገና ዛፉ ስር ያስቀምጣሉ። አዳኝ ምን አይነት ስጦታዎችን ሰጥቷችኋል? የራሳችሁን የገና ዛፍ ከስሩ ከአምስት ስጦታዎች ጋር ሳሉ። ከታች ያሉትን የቅዱሳት መጻህፍት ጥቅሶች አንብቡ እና ለእያንዳንዱ ጥቅስ አንድ ስጦታን በአንድ ቀለም ቀቡ። ሌሎችን ለመርዳት መንገዶችን በማግኘት ለኢየሱስ ስጦታዎ ችን መልሳቹ መስጠት ትችላላችሁ።

መዝሙር 33፥6

ዮሀንስ 14፥27

ዮሀንስ 15፥9

2 ኔፊ 2፥8

3 ኔፊ 15፥9

© 2014 በ Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ)
*First Presidency Message, December 2014.* Amharic. 10872 506 ትርጉም

# የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ሚስኦን፥ የሰላም ልዑል

እምነት፤ ቤተሰብ፤ እርዳታ

*በጸሎት መንፈስ ይህንን መረጃ አንብቡት እና ምን እንደምታካፍሉ ለማወቅ ጣሩ። የአዳኝን ህይወት እና ተልእኮ መረዳት በእርሱ ያላችሁን እምነት የሚያሳድገው እና በሴቶች የቤት ለቤት ትምህርት ምክንያት የምትንከባከቧቸውን የሚባርከው እንዴት ነው? ለተጨማሪ መረጃ ወደwww.reliefsociety.lds.org።*

*ይህ የአዳኝን ተልዕኮ ሁኔታዎችን የሚያስመለክቱ የተከታታይ የሴቶች የቤት ለቤት ትምህርት መልእክቶች ክፍል ነው።*

የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ኲዊንት ኤል ኩክ የአስራሁለት ሐዋሪያት ጉባኤ አባል እንዳሉት "አዳኝ እውነተኛ የሰላም ምንጭ ነው"። "በህይወት ፈተናዎች ውስጥም፣ በክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ እና በእርሱ ጸጋ ምክንያት፣ የጻድቅ ኑሮ በግል ሰላም ይሸለማል።"[1] ኢየሱስ ክርስቶስ የሰላም ልዑል መሆኑን መረዳት ውስጣዊ ሰላምን እንድናገኝ እና በእርሱ ያለንን እምነት እንድንጨምር ሊረዳን ይችላል።

ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ፥ "በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲኖራችሁ ይህን ተናገሬአችኋለው። በአለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ አለምን አሸንፌዋለሁ"(ዮሐንስ 16፥33)። ያንን እውነታ በመመስከር፣ የአጠቃላይ ሴቶች መረዳጃ ማህበር አመራር ሁለተኛ አማካሪ ሊንዳ ኤስ ሪቭስ እንዲህ አለች፥ "ጌታ ለእኔ መሀሪ ሆኗል እንዲሁም ሸክሞቼ ቀላል እንዲሆኑ አግዞኛል። ታላቅ ሰላም እንዲሰማኝ አግዞኛል።"[2]

የአስራ ሁለት ሐዋሪያት ጉባኤ አባል የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሪቻርድ ጂ ስካት እንዲህ አስተማሩ፥ "ለሰላም መልካም ቦታ ቢኖር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መአከላዊ ለማድረግ የምንችለውን ሁሉ ባደረግንበት በገዛ ቤቶቻችን ግድግዳዎች ውስጥ ነው።"[3]

## *ተጨማሪ ጥቅሶች*

ኢሳያስ 9፥6 ፤ ሉቃስ 2፥14፤ ዮሐንስ 14፥27፤ 1 ኔፊ 13፥37፤ ት እና ቃ 59፥23

## *ከቅዱሳት መጻህፍት*

ኢሳይያስ ስለሰላም ልዑሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ተነበየ (ኢሳይያስ 9፥6ተመልከቱ)። በአሜሪካዎች ውስጥ ላማናውያው ሳሙኤል ከአምስት አመት በኋላ ስለሚመጡት የክርስቶስን ውልደት ምልክቶች ተናገረ ሔለማን 14፥3፣ 5 ተመልከቱ )። የተተነበየለት ቀን ሲቃረብ፣ የማያምኑ ሰዎች እነዚህ ምልክቶች ባይከሰቱ ሁሉንም ክርስቲያኖች እንደሚገድሉ አስፈራሩ። ነቢዩ ኔፊ፣ "ቀኑን በሙሉ ወደ ጌታ በኃይል ጮኸ፤ እናም እነሆ፣ የጌታ ድምፅ እንዲህ እያል ወደ እርሱ መጣ፥ በሚቀጥለውም ቀን ወደ አለም እመጣለው" 3 ኔፊ 1፥12–13)። ምልክቶቹ ታዩ፣ እናም በክርስቶስ ውልደት፣ "ሰዎቹ በድጋሚ በምድሪቱ ሰላምን ማግኘት ጀመሩ" (ቁጥር 23)።

በቤተልሔም ውስጥ፣ ማሪያም "የበኩር ልጇዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በግርግምም አስተኛችው" (ሉቃስ 2፥7)።

ማስታወሻዎች

1. ኲዊንተን ኤል ኩክ፣ "Personal Peace: The Reward of Righteousness፣" *Liahona*፣ ግንቦት 2013 (እ.አ.አ)፣ 35።
2. ሊንዳ ኤስ ሪቭስ፣ "Claim the Blessings of Your Covenants፣" *Liahona*፣ ህዳር 2013 (እ.አ.አ)፣ 120።
3. ሪቻርድ ጂ ስካት፣ "For Peace at Home፣" *Liahona*፣ ግንቦት 2013 (እ.አ.አ)፣ 29።

## *ይህን አስቡበት*

*አዳኝ በምን አይነት መንገድ ነው ሰላምን ወደ ሕይወታችሁ የሚያመጣው?*

© 2014 በ Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ)
*Visiting Teaching Message, December 2014.* Amharic. 10872 506 ትርጉም